# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

### ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ››

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ አንባቢያን! ባለፈው ሳምንት ጽfከፋችን በተቋሙ ‹‹የኃይል ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ ስር›› የተቋቋመው የራስ ኃይል ኮንስትራክሽን ቢሮ በአዋሽ 2 እና 3 ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች እያከናወናቸው ስላሉ ዘርፈ ብዙ የመንገድ ጥገናዎች ማስነበባችን የሚታወስ ነው።

በዛሬ ዝግጅታችን ደግሞ ይሄው የሥራ ክፍል በአዳማ ቁጥር 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ እያከናወነ ስላለው የመንገድ ጥገና እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ ከመንገድ ጥገናው እያገኘ ስላለው በረከት የምናስነብባችሁ ይሆናል።



ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሥራ እድል የፈጠረው የመንገድ ጥገና

በራስ ኃይል ኮንስትራክሽን ቢሮ የሲቪል ጥገና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ግርማ መንገሻ እንደሚያስረዱት በአዳማ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ (wind power plant) በተገነባበት አካባቢ እየተጠገነ ያለው መንገድ 17 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ 14 ኪሎ ሜትሩ ወይም 90 በመቶ የሚሆነው ተጠናቋል።በዕቅዱ መሠረት የ2015 በጀት ዓመት ሳይጠናቀቅ ሠርቶ ለማስረከብ ተግተው እየሠሩ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪም ሌላ የሦስት ኪሎሜትር የጥገና ሥራ ተዋውለዋል። ቀደም ሲልም አዳማ አንድ ላይ የ12 ኪሎሜትር የመንገድ ጥገና ሥራ ሠርተው ማስረከባቸውን ኢንጂነር ግርማ ነግረውናል።

የሥራ ክፍሉ ኮንትራቱን የተፈራረመው ከተቋሙ የኃይል ማመንጫዎችና ኦፕሬሽን ጋር ነው።ኢንጂነር ግርማ እንደሚገልጹት ‹‹የሀገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› እንዲሉ የራስ ኃይል ኮንስትራሽን የሥራ ክፍል የተቋሙን ሥራ በራሱ የሰው ኃይል እያከናወነ ለጥገና ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ ወጪ እየታደገ ይገኛል፡ ፡የሥራ ክፍሉ ከተቋቋመ ጀምሮ ከተቋሙ የተለያዩ ዘርፎች ጋር የኮንትራት ውሎችን እየተፈራረመ የሲቪል ጥገና ሥራዎችን በመሥራት ‹‹ጥጃ ጠባ ሆድ ገባ›› እንዲሉ ለጥገና ተብሎ ከተቋሙ የሚመደበው ከፍተኛ በጀት ተመልሶ ወደ ተቋሙ ካዝና እንዲገባ የራሱን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል።

በአዳማ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ (wind power plant) በተተከለበት አካባቢ እየተጠገነ ያለው የሲቪል ጥገና ሥራ የ12 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ነው።ይህ ሥራ በውጭ የሥራ ተቋራጮች ይሠራ ቢባል እጥፍ ወጪ ሊጠይቅ እንደሚችል ሥራ አስኪያጁ ይናገራሉ።

ተቋሙ የራሱን ሥራ በራሱ የሰው ኃይል ማከናወን መቻሉ ወጪን ከማስቀረት ባሻገር ለጥገና ሥራዎች አፋጣኝ ምላሽ የመስጠትና ልምዶችን እየቀመረ አቅሙን የማሳደግ ዕድል አግኝቷል።

መንገዱ የአዳማ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ሠራተኞች በተለያዩ ቦታዎች ተተክለው የሚገኙትን የንፋስ ተርባይኖች እየተዟዟሩ ለመፈተሽ እና ለመቆጣጠር እንዲያስችላቸው ታስቦ የተገነባ ቢሆንም "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ " እንዲሉ የአካባቢው ማኅበረሰብ የመንገድ መሠረተ ልማት ጥያቄም ጭምር የመለሰ ነው።

ኢንጂነር ሹሚ ገለታ በአዳማ 2 የመንገድ ጥገና ሳይት ኢንጂነር ነው።ወጣቱ ኢንጂነር ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ምሕንድስና ተመርቆ ተቋሙን ከተቀላቀለ ጥቂት ዓመታትን አስቆጥሯል።በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ በሳይት ኢንጂነር ደረጃ ኃላፊነት ወስዶ በመሥራት ልምዶችን እያዳበረ እና ለሥራ ክፍሉ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ይገልጻል።

በጥገና ሥራው ቀደም ሲል ያልነበሩ ሦስት መንገድ አቋራጭ የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች (ፎርዶች) መሠራታቸውን እና ሦስት ኪሎ ሜትር አዲስ የጠጠር ንጣፍ መንገድ ለመሥራት መዘጋጀታቸውን ይናገራል።በዚህም ከዕለት ወደ ዕለት የራሱም ይሁን የሥራ ክፍሉ የመፈጸም አቅም እያደገ መምጣቱን ገልጿል።

የኃይል ማመንጫ ጣቢያው በአካባቢው በመገንባቱ ምክንያት "ቀጨማ፣ ቡቢሳና ኩሳዬ" የተባሉ ሦስት የገጠር ቀበሌዎች በመንገድ ኔት ወርክ ተሳስረዋል።ተሽከርካሪዎችም ወደ መንደሮቹ መግባት መውጣት ጀምረዋል።ይህም ነዋሪዎቹ ለዘመናት ወደ አዳማ እና ሞጆ ከተሞች ለመሄድ ረዥም መንገዶችን በእግራቸው ይጓዙ የነበረውን ድካም አስቀርቷል። የመንገድ ሥራው ለአንዳንዶቹ የአካባቢው ነዋሪዎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጥሮላቸዋል።

አቶ ፍቃዱ ነጋሽ የሥራ እድል ተጠቃሚ ከሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች አንዱ ናቸው።በአዳማ ወረዳ ሙክዬ ሃሮ ቀበሌ መንደር ነዋሪ የሆኑት እኚሁ ሰው ባለትዳር እና የአራት ልጆች አባት ናቸው።የሰዎችን መሬት የእኩል እያረሱ ቤተሰቦቻቸውን እንደሚያስተዳድሩ ይገልጻሉ።የግብርና ሥራ በማይኖር ሰዓት ደግሞ ወደ ከተማ እየሄዱ የቀን ሥራ በመሥራት ኑሯቸውን ይደጉማሉ።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በአካባቢያቸው በሚያከናውነው የመሠረተ ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ከመንደራቸው ሳይርቁ የጉልበት ሥራ በመሥራት በቀን 200 ብር በወር ከ5ሺህ እስከ 6ሺህ ብር እያገኙ መሆኑን ይናገራሉ። ጣቢያው ለሀገር ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ በተጨማሪ ለግለሰቦችም የሥራ ዕድል በመፍጠር በሉል ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ነው።

ይሁንና ይላሉ አቶ ፍቃዱ ‹‹የመንገድ ጥገና ሥራው በመኖሩ በጉልበት ሥራ ተሰማርቼ ገንዘብ እንዳገኝ እድል የፈጠረልኝ ቢሆንም ከምንም በላይ የምደሰተው በመንገዱ መሠራት ነው።›› ምክንያታቸው ደግሞ ቀደም ሲል ነፍሰ ጡሮችን እና ታማሚዎችን በቃሬዛ ተሸክሞ ወደ አዳማ እና ሞጆ ከተሞች መውሰድ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ትልቅ ፈተና ነበር።መንገዱ ከተሠራ ወዲህ ግን ተሽከርካሪዎች እንደልብ ወደመንደራቸው ዘልቀው መግባት በመቻላቸው የጣቢያው መኖር ተራራ የነበረው ችግራቸውን እንዲናድ አድርጎላቸዋል።

የመንገድ ጥገናው ሲጀመር በጎልበት ሥራ እንዲሳተፉ ያደረጋቸው በሚሠሩት ሥራ ገንዘብ ማግኘታቸውን በማሰብ ብቻ ሳይሆን መንገዱ ምን ዓይነት ጠቀሜታ ወይም አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበር በመገንዘባቸውና እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚመለከቱት በመሆኑ ቶሎ ተጠግኖ ወደሥራ እንዲገባ ካላቸው ፍላጎት እንደሆነም ነግረውናል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ